**<u>የተጠንቀቅ ማሳሰቢያ ጥሪ</u>**

የሉሲ፤ ማለትም የመጀመሪያዋ የሰው ዝርያ ግኝት-አፅም፤ ለዋሸንግተን ስቴት ነዋሪዎች በኤግዚብሽን መልክ ኦክቶበር 4 በሲያትል ሴንተር ለሕዝብ መታየት ትጀምራለች። ሉሲ ወይንም በኢትዮጵያኖች አጠራር ድንቅነሽ በመባል የምትታወቀው የአፅም ግኝት በሂውስተን ከተማ ለሕዝብ ስትታይ ቆይታ አሁን ደግሞ በሲያትል ፓሲፊክ ሳይንስ ሴንተር አማካኝነት ወደከተማችን መጥታለች።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደረሰን እስካሁን ባልተረጋገጠ መረጃም መሠረት በመክፈቻው ቀን የኢትዮጵያ ጠ/ሚንስቴር ወይንም ፕሬዘዳንቱ እንደሚገኙ በሰፊው እየተወራ ነው። ለዚህም ይመስለናል በከተማችን የሚገኙት የዘረኛውንና የዲክታተሩን መንግሥት የፓለቲካ ተቃዋሚ ድርጅቶች ተከታታይ ስብሰባ አድርገው ተቃውሞአቸውን በከፍተኛ ድምፅ በአንድነት ለማሰማት ተስማምተው የተነሱት።

በሲያትል የሚገኙት የተቃዋሚ ድርጅቶች ተወካዮች ባለፈው ዓመት አዲሱ ለገሠ፤ የወያኔ ም/ጠ ሚኒስተር በመጣ ጊዜ ከተማውን ያናጋ ጠንካራ የተቃውሞ ስብስብና ሰልፍ በመካሄዱ እንግዳው በሚያሳፍር ሁኔታ በጉአሮ በር ሾልኮ እንዳመለጠ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው።

ተቃውሞውን ከሚያስተባብረው ሀይል በተገኘው መረጃ መሠረት የሲያትል ሕዝብ ወገኖቻችን በረሀብ ሲረግፉ ረሀብ የለም በማለት፤ የሰብ ዓዊ መብቶችን በመሣሪያ ኀይል ረግጦ የያዘና፤ በዘርና በሀይማኖት ከፋፍሎ ሕዝባችንን የሚያጨራርስ መሪ ቢያችን ሲመጣ አሳፍረን መመለስ የሚጠበቅብን ነው። ለዚህም ተጨማሪ መረጃና አስፈላጊውን ዝግጅት አድርገን እስከምናስታውቃችሁ ድረስ በተጠንቀቅ እንድትጠብቁን አደራ እንላላን።

አስተባባሪዎች

EthioLion.Com